First Priority student & Youth Ministry

ፈርስት ፕራዮሪቲ ስቱደንት ኤንድ ዩዝ ሚኒስትሪ

መተዳደሪያ

ደንብ

ታህሳስ 2015ዓ.ም
አዲስ በባ ኢትዮጵያ

ማውጫ

አንቀጽ አንድ፡ መመስረት 4

አንቀጽ ሁለትት፡ ስያሜ 5

አንቀጽ ሦስት፡ ትርጉም 5

አንቀጽ አራት፡ የልጎ አርማ 5

አንቀጽ አምስት፡ አድራሻ 6

አንቀጽ ሰድስት 6

የእምነት አቋም (ዶክትሪን) 6

አንቀጽ ሰባት፡ ራዕይ፣ ተልኮ፣ ግቦችና ዕሴቶች 7

ራዕይ ፡- የክርስቶስ ተስፋ በትውልድ ላይ ማየት 7

ዘርፎቻችን 7

- አንኳር ግቦች፡ 8
- የአጭር ጊዜ ግብ፡ 8
- የመካከለኛ ጊዜ ግብ፡ 8

አንቀጽ ስምንት፡ የፈርስት ፕራዮሪቲ ስቱደንት ኤንድ ዩዝ ሚኒስትሪ የገቢ ምንጮች 9

አንቀጽ ዘጠኝ፡ አስተዳደራዊ መዋቅር 10

አንቀጽ አስር፡ የጠቅላላ ጉባዔ ስልጣንና ተግባራት 11

አንቀጽ አስራ አንድ፡ የጠቅላላ ጉባዔ አመራር አካላት ስልጣንና ተግባር 11

አንቀጽ አስራ ሁለት፡ የጠቅላላ ጉባዔ ስብሰባ የምርጫና የውሳኔ አሰጣጥ ሥኑ ሥርዓት 11

አንቀጽ አስራ ሦስት፡ የሥራ አመራር ቦርድ ሥልጣንና ተግባር 12

አንቀጽ አስራ አራት፡ የሥራ አመራር ቦርድ አባላት እና የአመራር አካሊት ስልጣንና ተግባር 12

አንቀጽ አስራ አምስት፡ የሥራ አመራር ቦርድ የስብሰባ የድምጽ አሰጣጥ ሥኑ ሥርዓትና የቦርድ አባላት የአገልግልት ዘመን 13

አንቀጽ አስራ ሰድስት፡ የባለራዕይ ተግባርና ኃሊፊነት 13

አንቀጽ አስራ ሰባት፡ የሒሳብ ሹም ተግባርና ኃሊፊነት 14

አንቀጽ አስራ ስምንት፡ የገንዘብ ያዥ ኃሊፊነትና ተግባር 14

የኢትዮጵያ የወንጌል አማኞች አብያተ ክርስቲያናት ካውንስል
Ethiopian Council of Gospel Believer's Churches

አንቀጽ አስራ ዘጠኝ፡ የሚኒስትሪው የበጀት ዓመት 15
አንቀጽ ሃያ፡ ያለ መግባባት ወይም የማጭት አፈታት 15
አንቀጽ ሃያ አንድ፡ መተዳደሪያ ደንቡን ለማሻሻል 15
አንቀጽ ሃያ ሁለት፡ የሥጋ የጋብቻና የዝምድና ሁኔታ 15
አንቀጽ ሃያ ሶስት፡ መልካም ከርስቲያናዊ ተግባራት 15
አንቀጽ ሃያ አራት፡ ተፈፃሚነት 16
አንቀጽ ሃያ አምስት፡ መተዳደሪያ ደንቡ በሚፀናበት ጊዜ 16

ፈርስት ፕራዮሪቲ ስቱደንት ኤንድ ዩዝ ሚኒስትሪ

First Priority student & Youth Ministry

መተዳደሪያ ደንብ

መግቢያ

ፈርስት ፕራዮሪቲ ስቱደንት ኤንድ ዩዝ ሚኒስትሪ የክርስቶስ አካል ሲሆን የተረጋገጠ ስትራቴጂን በመጠቀም በማህበረሰብ ውስጥ ወጣትና ተማሪ ሚስዮናውያ በማፍራትና ሁለንተናዊ አገልግሎት በመስጠት የክርስቶስ ተስፋ ትውልድ የሚያደርስ ሚኒስትሪ ነው።

አንድ ሰው የሆነ ሥራ እንዲሠራልን ከመወሰናችን በፊት ግለሰቡ ብቃት ያለው መሆኑን እናጣራለን። የተረጋገጠ የሙያው ማረጋገጫ ያለው መሆኑን እናረጋግጣለን። ለምሳሌ:- ዶክተር፣ የጥርስ ሐኪም፣ የሕግ ባለሙያ፣ መምህር፣ ኮንትራክተር፣ ወዘተ ከታወቀ ተቋም ማረጋገጫ ከልለው አገልግሎት እንዲሰጠን አይፈቀድለትም። ይህ በመሆኑ አንድ ሰው ሥራውን እንዲሠራ ከመስጠታችን በፊት ያንን ግለሰብ "የተመረቅ" ወይም ሕጋዊ ፈቃድ ያለውም መሆኑን እናረጋግጣለን።

የኢየሱስ ክርስቶስ ተከታይ በመሆን ወንጌልን ለትውልድ የማዳረስ ሥራ አስፈላጊነት ከዚህ ያነሰ አይደለም። እንደ እውነቱ ከሆነ በትውልድ ላይ የሚሰራው ሥራ ምድራዊ ውጤት ብቻ ሳይሆን ዘላለማዊ ውጤት ወይም መዘዝ ያለው ነው። ቀጣዩ ትውልድ የክርስቶስን ተስፋ እንዲኖርና እንዲያካፈል ትኩረት መስጠት ትርፍ ጉዳይ ሳይሆን ቅድሚያ የሚሰጠው ዋና ነገር ነው። ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን በትልድ መሃል ለማክበር በደንብ መዘጋጀት ያስፈልጋል።

ስለዚህ እንደ ፈርስት ፕራዮሪቲ ስቱደንት ኤንድ ዩዝ ሚኒስትሪ **በትውልድ ላይ ለመስራት** ብቁ መሆን ያስፈልጋል ብሎ ያምናል። ምክንያቱም **ፈርስት ፕራዮሪቲ ስቱደንት ኤንድ ዩዝ ሚኒስትሪ** ስትራቴጂን የሚተገብር ወይም በትውልድ ላይ የሚሰራ እያንዳንዱ የአገልጋይ በጥራት፣ በወጥነት፣ በውጤታማነትና በተጠያቂነት እንዲሰራ **ፈርስት ፕራዮሪቲ ስቱደንት ኤንድ ዩዝ ሚኒስትሪ** ይፈልጋል። እኛ ለኢየሱስ ክርስቶስ በደንብ ምርጥ አድርገን ብንሰራለት ይበዛበታል ወይ? እርቃኑን መስቀል ላይ ለተንጠለጠለልን አሳምረን ብንሰራለት አይበዛበት። ቆላስይስ 3:17 & 23

ለትውልድ የሚሳቡ የበቁ ወጣቶችንና የየወጣት አገልጋዮችን በማፍራት የወንጌልን ሥራ ለማዛለቅ ፈርስት ፕራዮሪቲ የት/ቤትና የወጣት አገልግሎት ጠንክሮ ለመስራት የቆመ ድርጅት ነው።

እግዚአብሔር የወንጌልን ማዕበል በምድራችን በወጣቶች ሲያነሳሳ አንዳንዶቻችን የተቋደስነው ልሎቻችን ደግሞ ስንሰማ ያደግነው እውነት ነው። ዛሬ በየአብያተ ክርስቲያናት መጋቢዎችና አገልጋዮች ከሆኑት አብዛኛዎቹ በወጣትነት ዕድሚያቸው ጌታን ተቀብለው በውስጣቸው ያለውን የፍቅሩን ንዳድ ለዓለም ለማድረስ የቆረጡ ወጣቶች የነበሩ ናቸው።

ወጣቶች ላይ ትኩረት ከማድረግ ይልቅ ተራ እና እግዚአብሔርን በማያሳስበው ጉዳይ ላይ ትኩረት ማድረግ ኪሳራው ብዙ ነው። ለወጣት አገልግሎት በቂ በጀት ከመመደብ ይልቅ ትልቅ ያላገናዘቡ ሕንጻዎች ላይ ማተኮር ለአውሮፓም አልጠቀማቸውም።

የኢትዮጵያ የወንጌል አማኞች አብያተ ክርስቲያናት ጉባኤ
Ethiopian Council of Gospel Believer's Churches

ከ6000 እስከ 10,000 የሚደርሱ የማምለኪያ አዳራሾች በዓመት ውስጥ እንደሚዘጉ መረጃች ያሳያሉ አንዳንዶች ለሲኒማ ቤቶች፣ለመሰብሰቢያ አዳራሽነትና ለጭፈራ ቤቶችም እየተሸጡ ነው።

አፍሪካ ብሎም ኢትዮጵያ የወጣት አገር ናት። USAID እ.ኢ.አ በ2017ዓ.ም ባወጣው መግለጫ በኢትዮጵያ ውስጥ ካለው ማህበረሰብ ከመቶ አርባ አንድ ያህሉ ከአሥራ አምስት ዓመት ዕድሜ በታች የሆኑ ወጣቶች መሆናቸውን እና ከሃያ ስምንት ከመቶ የሚበልጡት ደግሞ ዕድሜያቸው ከአሥራ አምስት እስከ ሃያ ዘጠኝ ዓመት ዕድሜ ክልል ያሉ ወጣቶች መሆናቸውን አስፍሯል (USAID, 2017)።

አህጉራችን ብሎም በአገራችን በኢትዮጵያ በጉልህ ወጣት ቁጥር የተሞላች በመሆኗ ወጣቶች ላይ አለመሥራት አገር ላይና በቤተ ክርስቲያን ላይ አለመሥራት ይሆናል። እንዲሁም ልሎች ጥናቶች የሚያሳዩት ከማህበረሰቡ አብዛኛውን በወጣት ዕድሜ ክልል እንደሚገኝ እንደሆነ ነው። ይህ ቁጥር አንዳንድ ጊዜ እስከ 70% ይደርሳል። ይህ ነባራዊ እውነታ በቤተ ክርስቲያንያን ውስጥ ስለሚንጸባረቅ በዚህ ከፍተኛ ቁጥር ለሆኑ ወጣቶች ትኩረት መስጠት ብልህነት ነው።

በአገራችን በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ወጣቶች ይገኙበታል። ኢየሱስ ክርስቶስ የአንድ ሰው ጉዳይ ያሳስበውና ግድ ይለው ነበር። ቃሉም ሲናገር በአንድ ሰው መዳን ምክንያት በሰማያት ታላቅ ደስታ ይሆናል ይላል። ዮናስን ያሳስበው የነበረው የግሉና የዘሩ ምቾት ነበረ። እግዚአብሔር ግን የህዝብ ሁሉ ጉዳይ ያሳስበዋል። "እግዚአብሔርም፡-አንተ ትበቅል ዘንድ ላልደከምክበት ላላሳደግካትም በአንድ ልሊትም በደረቀችው ቅል አዝነሃል።እኔስ ቀኛቸውን ግራቸውን የማይለዩ ከመቶ 45 ሺህ የሚበልጡ ሰዎችና ላሉባት ለታላቂቱ ከተማ ለነነዌ አላዝንምን አለው።" (ዮና4፡10)። እነዚህ በብዙ ቢሊዮኖች የሚቆጠሩ ወጣቶች እግዚአብሔርን ያሳስበዋል። እግዚአብሔርን የሚያሳስበው እኛንም ሊያሳስበን ይገባል።

ወጣቶች ላይ መስራት ችላ ሊባል የማይገባ ጉዳይ መሆኑን ከላይ ያየናቸው መረጃዎች ጠቁመውናል። ወጣቶች ላይ መስራት ትዕግስትና መሰጠትን ይጠይቃል። በተለመደው መልኩ መቀጠል ቀላል ነው። ነገር ግን ውጤታማ ለመሆን ተጨማሪ ርቀቶችን መሄድ የሚጠይቅ ቢሆንም ፍሬያማ ያደርገናል። ወጣቶችን ችላ ማለት ከማህበረሰቡ ከግማሽ በላይ ችላ እንደማለትነው። ስለዚህ ነቅተን መነሳት አለብን። በብልሀትና ፍሬያማ በሚያደርገን አካሄድ መሄድ አለብን። ትንሽ ገንዘብና ጉልበት አውጥተን በእግዚአብሔር መንግስት ውስጥ ብዙ ነፍሳት የሚድኑበትን ስልት መከተል አለብን።

ፈርስት ፕራዮሪቲ የት/ቤትና የወጣት አገልግሎት ከአብያተ ክርስቲያናት ጋር ማለትም ከክርስቶስ አካል ጋር በወንጌልና በትውልድ ጉዳይ ላይ በጋራ ይሰራል። ማህበረሰቡ ለትውልድ በጎ አስተዋጽዖ የሚያበረክትበትን ሁኔታዎች ያመቻቻል። በየአገሩ ካሉ ማላጆች ጋር አብሮ ይሰራል።

በአጠቃላይ ፈርስት ፕራዮሪቲ የት/ቤትና የወጣት አገልግሎት በጋራ፣ በጥራት፣ በወጥነት፣ በውጤታማነትና በተጠያቂነት በትውልድ ላይ ይሰራል።

አንቀጽ አንድ፡ መመስረት

ፈርስት ፕራዮሪቲ ስቱደንት ኤንድ ዮዝ ሚኒስትሪ የሐዲሳዊ ተጋቶ ኢትዮጵያ የወንጌል አማኞች አብያተ ክርስቲያናት ካውንስል መሠረት ህዲር 20/2015 ዓ.ም ተመስርቷል።

አንቀጽ ሁለትት፡ ስያሜ

በዚህ ደንብ አንቀጽ አንድ መሠረት የተመሰረተው የሃይማኖት ተቋም ፈርስት ፕራዮሪቲ ስቱደንት ኤንድ የዝ ሚኒስትሪ ተብሎ ይጠራል።

አንቀጽ ሦስት፡ ትርጉም

ፈርስት ፕራዮሪቲ ስቱደንት ኤንድ የዝ ሚኒስትሪ ተብሎ የተሰየመው ትርጉም የቅድሚያ ቅድኒያ ለትውልድ በተመሳሳይ መልኩ ለወንጌል እንደሚሰጥ ያመለክታል።

አንቀጽ አራት፡ የልጎ አርማ

First Priority student & Youth Ministry

ፈርስት ፕራዮሪቲ ስቱደንት ኤንድ ዩዝ ሚኒስትሪ

የአርማው ትርጉም

1. የውስጡ ቅርጽ ምስል ከሞተ ዓሣ የተገኘ ነው
2. ኢየሱስ ዓሣ አጥማጆችን ጠርቶ ሰዎች አጥማጆች እንዳደረጋቸው ለማመልከት ነው
3. በሞተ ዓሣ ዓይን ላይ የሚታየው የመስቀል ምልክት ለሰው ልጆች ሁሉ ተስፋ መስቀል ላይ የተሰራው ሥራ መሆኑን ያሳያል
4. እንዲሁም የተያያዙት የእንግሊዘኛ ፍደላት F እና P የተቋሙን ሥም ይገልጻሉ
5. ከውጭ ያለው ድርብ ሙሉ ክብ በትውልድ ላይ የሚሰራው ሥራ በጋራ የሚሰራ መሆኑን ያሳያል።

አንቀጽ አምስት፡ ኤድራሻ

ፈርስት ፕራዮሪቲ ስቱደንት ኤንድ የዝ ሚኒስትሪ ዋና ጽ/ቤት አዲስ አበባ ለሚ ኩራ አያት ኢ.ፓርትሜንት B39 የቤት ቁጥር 4012 እንደ አስፈላጊነቱ አዲስ አበባም ሆነ በልሎች ከልሎች ላይ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ይኖሩታል።

አንቀጽ ስድስት

የእምነት አቋም (ዶክትሪን)

የፈርስት ፕራዮሪቲ የእምነት መግለጫ

መጽሐፍ ቅዱስ፦ መጽሐፍ ቅዱስ ፍጹም የእግዚአብሔር ቃል ነው። ቅዱስና ፍጹም የሆነ እስትንፋሱ እግዚአብሔር ነው። እግዚአብሔርን እና ፈቃዱን ለማወቅ ከእግዚአብሔር የተሰጠ ብቸኛው ምንጭ እና የመጨረሻ ሥልጣን ያለው መጽሐፍ ነው። 2ኛ ጢሞቴዎስ 3፡15-16

ቤተ ክርስቲያን፦ እግዚአብሔር ዓላማውን ለመፈጸም የመረጠበት መንገድ በቤተክርስቲያን በኩል ነው። ቤተክርስቲያን የክርስቶስ አካል ናት። ቤተክርስቲያን ያለውን ማንኛውንም መንገድ በመጠቀም በሁሉም ቦታ እንደ አንድ ክርስቶስ አካል ትሰራለች። ኤፌሶን 2:2፣ 5፡25፣ ሮሜ 12፡4-5፣ 1 ቆሮንቶስ 12፡12-20

ሥላሴ፦ እግዚአብሔር አንድ አምላክ ነው። በዘላለማዊነት በሦስት አካላት የተገለጠው ነው። እርሱም እግዚአብሔር አብ፣ እግዚአብሔር ወልድ እና እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ አንድ አምላክ ነው። ማቴዎስ 28፡19

ኢየሱስ ክርስቶስ፦ ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ዘላለማዊ ልጅ ነው። በመንፈስ ቅዱስ ተፀንሶ ከድንግል ማርያም ተወለደ። ኃጢአት የሌለበትን ሕይወት ኖረ ከዚያም ኃጢአታችንን ሁሉ በመስቀል ላይ በራሱ ላይ ወሰደ። በመስቀል ላይ በመሞቱ እግዚአብሔር ለኃጢአታችን ያዘጋጀውን ቅጣት ከፈለ። ከመቃብር ተነስቶ ወደ ሰማይ ተመልሶ በሰማያት ባለው አብ ቀኝ ተቀምጦ አማላጃችን እና ጠበቃ ሆኖ እየሰራ አለ። በሰው ልጆች፣ በሕያዋንና በመ·ታን ላይ ሊፈርድ ወደ ምድር ይመለሳል። ከዚያም ዘላለማዊ መንግሥት እንደ ቃሉ ይመሠርታል። ዮሐንስ 1፡14፣ ማቴዎስ 1፡20-21፣ ዕብራውያን 4፡14-16

መንፈስ ቅዱስ፦ ክርስቲያን ሁሉ ዳግም የተወለደው በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ነው። በእያንዳንዱ ክርስቲያን ውስት የእግዚአብሔር መገኘት እና በሕይወታቸው ውስጥ የመታደስ ኃይል በመንፈስ ቅዱስ ይኖራል። እያንዳንዱ ክርስቲያን በየቀኑ በመንፈስ ቅዱስ መሞላትና በመንፈስ ቅዱስ መመራት አለበት። ዮሐንስ 3:3-8፣ 14:26፣ የሐዋርያት ሥራ 2:38፣ 15፡8፣ 1 ቆሮንቶስ 6፡19፣ ኤፌሶን 5፡25፣

የኢትዮጵያ የወንጌል አማኞች አብያተ ክርስቲያናት ካውንስል
Ethiopian Council of Gospel Believer's Churches

ኃጢአት፦ ሰው ሁሉ ከእግዚአብሔር ተለይቷል እናም የቅዱስ እና ጻድቅ አምላክ ፍርድ ይጠብቀዋል። በየትኛውም ቦታ ያሉ ሰዎች ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር የመዋጀት ግንኙነት ውስጥ መግባት አለባቸው። ምክንያቱም ኢየሱስ ለሰው ልጅ ሁሉ ኃጢአት በቂ ክፍያ ፈጽሟል። ሮሜ 3፡23፣ ሮሜ 6፡23፣ ዕብ 9፡27

መዳን፦ ወደ መንግሥተ ሰማያት ለመግባት አንድ ሰው በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል የእግዚአብሔርን ፍቅር እና ይቅርታ መቀበል አለበት። ወደ እግዚአብሔር መቅረብ የሚቻለው ለሰው ሁሉ የተሰጠ እና የቀረበ በቀራንዮ መስቀል ላይ ደሙን ባፈሰሰው በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ብቻ ነው። ሮሜ 6፡23፣ ዮሃንስ 14፡6፣ 1 ጴጥሮስ 1፡18-21፣ ኤፌሶን 1፡7

መንግስተ ሰማያት፦ መንግሥተ ሰማያት እውነተኛ ቦታ ነው። በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ወደ እግዚአብሔር ለመጡ ሰዎች የዘላለም አጣ ፈንታ ነው። ዮሐንስ 14፡1-3፣ 2 ጢሞቴዎስ 4፡18

ሲዖል፦ ሲኦል ለዲያብሎስና ለኢጋንንቱ የተፈጠረ እውነተኛ ቦታ ነው። ያለ ክርስቶስ የሚሞቱ ሰዎች ሁሉ ለዘለአለም ወደ ገሃነም ይወሰዳሉ። ማቴዎስ 10፡28፣ 2ኛ ጴጥሮስ 2፡4

ደቀ መዝሙርነት፦ እያንዳንዱ ክርስቲያን ኢየሱስ ክርስቶስን ወደ መምሰል መለወጥ አለበት። ይህም ለክርስቲያን እጣ ፈንታው እንዲሆን የእግዚአብሔር ንድፍና ፍላጎት ነው። ሮሜ 8፡28-29፣ 1 ቆሮንቶስ 7፡1

ተልዕኮ፦ እያንዳንዱ ክርስቲያን ኢየሱስ ክርስቶስን ለማገልገል ራሱን መስጠት አለበት። በሕይወታችን ለእሱ ስልጣን መገዛት በሕይወታችን የእርሱ ዓላማ መፈጸም አለብን። ማቴዎስ 6:24፣ 16፡24፣ ያእቆብ 4፡7፣

አገልግሎት፦ እያንዳንዱ ክርስቲያን የተቀደሰ ክርስቲያናዊ ሕይወትን በመከተል ለሌሎች ሐዘኔታና ርኅራኄ ማሳየትና ለእያንዳንዱ ሰው ደኅንነት ሊጨነቅና ሌሎችን ከራሱ ሊያስቀድም ይገባዋል። ማቴዎስ 22፡37-39፣ ፊልጵስዩስ 2፡2-5፣

አንቀጽ ሰባት፡ ራዕይ፣ ተልኮ፣ ግቦችና ዕሴቶች

ራዕይ ፦ የክርስቶስ ተስፋ በትውልድ ላይ ማየት

ተልዕኮ፡ የክርስቶስን ተስፋ ለመኖር እና ለማካፈል ትውልድን ማስታጠቅ

ዘርፎቻችን

1. ከአቢያተ ክርስቲያን ጎብራቶች ጋር በጋራ መሥራት
2. የወጣቶች መር አገልግሎት
3. ማህበረሰብን መሰረት ያደረገ እና በአካባቢው ባለቤትነት የተያዘ
4. ከየአካባቢው ለአካባቢው የድጋፍ መዋቅር
5. በገጠር፣ በከተማ ዳርቻዎች እና በከተማ ቅንብሮች ውስጥ ሥራት

የኢትዮጵያ የወንጌል አማኞች አብያተ ክርስቲያናት ኅብረት
Ethiopian Council of Gospel Believer's Churches

ዕሴቶቻችን

1. መጽሐፍ ቅዱስ የበላይነት
2. የክርስቶስ አካል አንድነት
3. የመንፈስ ቅዱስ አጋዥነት
4. የትውልድ ክቡርነት
5. የጽሞና ጊዜ
6. ተስጥዖዎችንና የጸጋ ሥጦታዎችን ማሳደግ

አንኳር ግቦች፡

i. ትውልድ የክርስቶስን ተስፈ እንዲኖር ለመርዳት በየት/ቤቱ የመረጃ ቋት በመሰብሰብ በጎዋስ ቡድን መያዝ
ii. የቅዱሳን አዳኒ ወጣት ጎብረቶችን በእያንዳንዱ የክርስቶስ አካል በሆነች ቤተ ክርስቲያን በሉበት ማጠናከር በልላበት እንደ አዲስ ማስጀመር
iii. የቅዱሳን አዳኒ ወጣት ጎብረቶችን በእያንዳንዱ ት/ቤት ማስጀመር
iv. በእያንዳንዱ አጥብያ ለአዳኒ ወጣት አገልግሎት ቋሚ አገልጋይ እንዲመድቡ ማንዛቤ መፍጠር
v. በእያንዳንዱ ት/ቤት ተማሪ አገልግሎት አንድ የሙሉ ጊዜ አገልጋይ መመደብ
vi. በወጣት አገልግሎት ከሰርተፊኬት እስከ ዲግሪ ድርስ ሥልጠናዎችን መስጠት

የአጭር ጊዜ ግብ፡

ሀ. በ2015 በተለያዩ ሀገራችን ክፍሎች የማስጀመር ሥራ ማከናወን።
ለ. በ2015 በአዲስ አበባ፣ አዳማ፣ ሀዋሳ፣ ባህርዳር ከተሞችን ማሰልጠን።
ሐ. 10 አገልጋዮችን ማብቃትና በተመረጡ ት/ቤቶች መሾም
መ. ሚኒስትሪውን የማስተዋወቂያ ፕሮግራም በሚድያ፣ በሶሻል ሚዲያ፣ በስሚናር ማካሔድ።
ረ. ስለ ወጣት አገልግሎትና ስለ ስኩል ሚሽን በሰርትፍኬት ደረጃ ሥልጠና መጀመር

የመካከለኛ ጊዜ ግብ፡

ሀ. በሚቀጥሉት 5ዓመታት ሚኒስትሪውን ከጫፍ እስከ ጫፍ ማስተዋወቅ
ለ. ከተለያዩ ሀገራት ወጣቶችን በመጋበዝ ልምድ ልውውጥ ማድረግ
ሐ. ከኢትዮጵያ ወደተለያዩ ሀገራት ወጣቶችን በማላክ ለወንጌል ሥራ ማነቃቃት
ሰ. ከ 2015 እስከ 2020 ባሉ ዓመታት እስከ 100 የት/ቤት አገልጋዮችን መቅጠር
ረ. በየክልሉ የሚኒስትሪው ቢሮ መክፈት
ሸ. ስለ ወጣት አገልግሎትና ስለ ስኩል ሚሽን በዲግሪ ደረጃ ማሰልጠን መጀመር

የረጅም ጊዜ ግቦች፡

ሀ. የሚኒስትሪው ማዕከል መገንባት

የኢትዮጵያ የወንጌል አማኞች አብያተ ክርስቲያናት ካውንስል
Ethiopian Council of Gospel Believer's Churches

ሉ. በየት/ቤቱ በነፍስ ወከፍ አንድ አገልጋይ መመደብ

ሐ. በት/ቤት የሚሠራውን ሥራ በመሪነት መሥራት

መ. ሰለ ወጣት አገልግሎትና ስለ ስኩል ሚሽን በማስተርስ ደረጀ ማሰልጠን መጀመር

አንቀጽ ሰምንት፡ የፊርስት ፕራዮሪቲ ስቱደንት ኤንድ ዩዝ ሚኒስትሪ የገቢ ምንጮች

ፊርስት ፕራዮሪቲ ስቱደንት ኤንድ ኡዝ ሚኒስትሪን ገቢ የሚያገባቸው ዋና ዋና መንገዶች የሚከተሉትን ይመስላሉ፤

1. የመጽሐፍት ሽያጭ
2. የስልጠና ክፍያ
3. የስልጠና ግብዓቶች ሽያጭ
4. ከኢጋሮች በሚገኝ ስጦታ
5. ገቢ ማሰባሰቢያ ልዩ ዝግጅቶች
6. ሰሊማዊና ህጋዊ ከሆኑ ድጋፍ ሰጪ ግለሰብና ድርጅት ገቢዎች ይኖሩታል

አንቀጽ ዘጠኝ፡ አስተዳደራዊ መዋቅር



አንቀጽ አስር፡ የጠቅላላ ጉባዔ ስልጣንና ተግባራት

ጠቅላላ ጉባዔው የሚከተሉትን ስልጣን እና ተግባሮች ይኖሩታል።

1. ጠቅላላ ጉባዔው ሰብሳቢ፣ ምክትክ ሰብሳቢ፣ ጸሐፊ፣ የሥራ አመራር ቦርድ አባላትንና ኦዲተር ይመርጣል/ ይሽራል፣
2. በሚኒስትሪው የፖሊሲ አቅጣጫ ላይ ውሳኔ ይሰጣል።
3. ዓመታዊ የሥራ ዕቅድ፣ የዕቅድ አፈፃፀም እና የኦዲት ሪፖርት ይሰማል መርምሮ ያፀድቃል።
4. ፊርስት ፕራዮሪቲ መተዳደሪያ ደንብ ያሻሽላል
5. ፊርስት ፕራዮሪቲ መተዳደሪያ ዋና ጽ/ቤት እና ቅርንጫፍ በሚከፈትበት ሁኔታ ላይ ይወስናል፣
6. ፊርስት ፕራዮሪቲ መተዳደሪያ ሚኒስትሪ ሂሳብ በውስጥ ወይም በውጭ ኦዲተር እንዲመረመር ያደርጋል፣
7. ፊርስት ፕራዮሪቲ መተዳደሪያ ሀብትና ንብረት አስተዳደራዊ ጉዳይ ላይ የመጨረሻ ውሳኔ ይሰጣል፣
8. ፊርስት ፕራዮሪቲ መተዳደሪያ አመራር አካል የተሰጡትን ጉዳዮች ይወስናል።

አንቀጽ አስራ አንድ፡ የጠቅላላ ጉባዔ አመራር አካላት ስልጣንና ተግባር

የጠቅላላ ጉባዔው ሰብሳቢ ምክትል ሰብሳቢ እና ጸሐፊው የጠቅላላ ጉባዔው አመራር አካሊት ሲሆኑ ሥልጣንና ተግባራቸውን የሚከተለው ነው።

የጠቅላላ ጉባዔ ሰብሳቢ

1. ጠቅላላ ጉባዔው የሚያመጣቸውን ደንቦችና የሚሰጣቸውን ውሳኔዎች በትክክል ሥራ ላይ መዋላቸውን ይከታተላል፣
2. ጉባዔው ያፀደቃቸውን የሥራ እና የኦዲት ሪፖርቶች ለሚመለከታቸው መንግስታዊ አካላትና መንግስታዊ ላልሆኑ አካላት እንዲደርሱ ያደርጋል፣
3. ለጉባዔው የሚቀርቡ ጉዳዮችን ቅደም ተከተል በማውጣት ለውይይት እንዱቀርቡ ለፀሐፊ አጀንዳ ያስይዛል፣

ምክትል ሰብሳቢው

ሀ.ሰብሳቢው በተለያዩ ምክንያቶች በማይኖርበት ጊዜ ሰብሳቢውን ተክቶ ይሰራል፣

ለ. ከሰብሳቢው በሚሰጠው መመሪያ መሠረት የጠቅላላ ጉባዔ ውሳኔዎች በትክክል መፈፀማቸውን ያረጋግጣል

አንቀጽ አስራ ሁለት፡ የጠቅላላ ጉባዔ ስብሰባ የምርጫና የውሳኔ አሰጣጥ ሥነ-ሥርዓት

1. የጠቅላላ ጉባዔው መደበኛ ስብሰባውን [illegible] ጊዜ የሚያካሂድ ሲሆን አስቸኳይ ጉዳዮች ሲገጥሙ አስቸኳይ ስብሰባ ሊጠራ ይችላል

የኢትዮጵያ ወንጌላውያን አማኞች አብያተ ክርስቲያናት ጉባኤ
Ethiopian Council of Gospel Believer's Churches

2. ከጠቅላላ ጉባዔው አባላት ከ10% በላይ በሚሆን ጥያቄ አስቸኳይ ስብሰባ ሊጠራ ይችላሉ፤
3. ምርጫ ሲደረግ መላው ጉባዔው እንደተሟላ ሦስት የአስመራጭ ኮሚቴ አባላት ተመርጠው ምርጫው እንዲካሄድ ያደርጋለ፤
4. አስመራጭ ኮሚቴው አስቀድሞ የምርጫ መመዘኛዎች በጉባዔው እንዲወስኑ አድርጎ ምርጫውን ያስፈፅማል፤
5. ከጠቅላላ መደበኛ 51% ሲገኝ ምልዓተ ጉባዔው ይሆናል፤ ይህ ሳይሟላ ቀርቶ ሁለተኛ ጥሪ በማድረግ ጥሪው በአግባቡ ለአባላት መድረሱ ሲረጋገጥ በተገኙት አባላት በጥሪው ላይ በተገለፀው አጀንዳ ላይ ብቻ ውሳኔ ይሰጣል፤
6. የአባላቱ ቁጥር ከመብዛታቸው የተነሳ የሚኒስትሪው አባላት በሙለ መሰብሰብ ባልቻለ ጊዜ በውክልና መሰብሰብ ይቻላል። የአውካከለም ሥነ-ሥርዓት በአገልግልቱ የውስጥ ደንብ ይወሰናል፤
7. የጉባዔው ውሳኔው የሚተሊለፈው በስብሰባው በተገኙት አባላት ድምጽ ብልጫ ሆኖ እኩል ድምጽ ሲኖር ሰብሳቢው የደገፈው ሃሳብ ተፈፃሚ ይሆናል።

አንቀጽ አስራ ሦስት፡ የሥራ አመራር ቦርድ ሥልጣንና ተግባር

የሥራ አመራር ቦርድ ተጠሪነቱ ለጠቅላላ ጉባዔው ሆኖ የሚከተለት ስልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል።

1. በጠቅላላ ጉባዔዎች የሚሰጡ ውሳኔዎችንና የሚወጡ እቅድች ተግባራዊ መደረጋቸውን ይቆጣጠራል/ይከታተሊል፤
2. ፊርስት ፕራዮሪቲ ፖሊሲ ለማውጣት ወይም ለማሻሻል የሚቀርቡ ሃሳቦችን ተቀብሎና አስፈሊጊ አስተያየቶችን ጨምሮ ውሳኔ እንዲሰጥባቸው በጠቅላላ ጉባዔ ያቀርባል፤
3. ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች አስፈሊጊ በሆኑ አካባቢዎች እንዲከፈቱ ለጠቅላላ ጉባዔ አቅርቦ ያስወስናል፤
4. የሥራ አፈፃፀም መርምሮ ካስተያየት ጋር ለጠቅላላ ጉባዔ ለውሣኔ ያቀርባል፤
5. ፊርስት ፕራዮሪ የአጭር፤ የመካከለኛና የረጅም ጊዜ እቅድና በጀት ላይ በመምከር ለጠቅላላ ጉባዔ ለውሳኔ ያቀርባል፤
6. የሥራ አመራር መመሪያ ያወጣል፤
7. አስቸኳይ የጠቅላላ ጉባዔ ስብሰባ የሚጠራበት ምክንያት ሲገጥም ጥሪ እንዲደረግ ይወስናል፤

አንቀጽ አስራ አራት፡ የሥራ አመራር ቦርድ አባላት እና የአመራር አካሊት ስልጣንና ተግባር

የሥራ አመራር ቦርድ አባላት

1. የሥራ አመራር ቦርድ አምስት አባላት ይኖሩታል፤
2. ቦርደ ሰብሳቢውና ምክትል ሰብሳቢውን ይመርጣል፤

የኢትዮጵያ የወንጌል አማኞች አብያተ ክርስቲያናት ካውንስል
Ethiopian Council of Gospel Believer's Churches

የሥራ አመራር ቦርዱ አመራር አካል ሥልጣንና ተግባር የሚከተለው ነው

የቦርዱ ስብሳቢ

3. የቦርዱን ስብሰባ በሊቀመንበርነት ይመራል፤
4. ቦርዱ ያሳለፋቸውን ስብሰባዎች በጠቅላላ ጉባዔ ያቀርባል፤
5. ቦርዱ ያወጣቸውን ፖሊሲዎችና መመሪያዎች ለጠቅላላ ጉባዔ አቅርቦ ያፀድቃል
6. ተጠሪነቱ ለጠቅላላ ጉባዔና ለቦርዱ ይሆናል፤

ምክትል ስብሳቢ

7. ስብሳቢው በተለያዩ ምክንያቶች በልለ ጊዜ ተክቶ ይሰራል፤
8. በስብሳቢው የሚሰጠውን ልሎች ሥራዎችን ያከናውናል፤

አንቀጽ አስራ አምስት፡ የሥራ አመራር ቦርድ የስብሰባ የድምጽ አሰጣጥ ሥነ-ሥርዓትና የቦርድ አባላት የአገልግልት ዘመን

የቦርድ መደበኛ ስብሰባ በዓመት አራት ጊዜ የሚከናወን ሆኖ አስቸኳይ ስብሰባ የሚያስፈልግበት ጊዜ ልዩ ስብሰባ ያደርግ ይችላሉ።

1. አስቸኳይ ስብሰባ በቦርዱ ሰብሳቢ ወይም በባለ ራዕይ ሊጠራ ይችላሉ።
2. ከአጠቃላይ ጉባዔ ከግማሽ በላይ ከተገኙ ምልዓተ ጉባዔው እንደተሟላ ይቆጠራል
3. ካልተሟላ ድጋሚ ጥሪ ይደረጋል፤ በድጋሚ በተደረገው ጥሪ ምልዓተ ጉባዔው ካልተሟሊ በተገኙት አባላት ስብሰባው ሊካሄድ ይችላሉ።
4. ውሳኔዎች በድምጽ ብልጫ ይተሊለፋለ፤ እኩል ሲሆን ሰብሳቢው የደገፈው ሐሳብ ይፀናል።
5. የቦርድ አባላት አገልግልት ዘመን ለሦስት ዓመት ይሆናል።
6. ከዋና መጋቢው በስተቀር ልሎች የቦርድ አባላት ያለ ደመወዝ ያገለግላሉ።
7. የቦርድ አባላት በድጋሚ ለሦስት ዓመት ሊመረጡ ይችሊለ። ከዚያ በኋሊ ግን ለአንድ የቦርድ ዘመን ያርፋለ።

አንቀጽ አስራ ስድስት፡ የባለራዕይ ተግባርና ኃሊፊነት

የሚከተለት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል።

1. በማንኛውም አካል ዘንድ ፊርስት ፕራዮሪቲ ስቱደንት ኤንድ ዩዝ ሚኒስትሪን ይወክሊል፤ የፊርስት ፕራዮሪቲ ሥራ በተመለከተ ማንኛውንም ጉዲይ ይፊፅማል፤ ውክልና ይሰጣል፤ የፊርስት ፕራዮሪ ስም የደብዲቤ ልውውጦችን ያደርጋል፤ የጠቅላላ ጉባዔውን ወይም የቦርዱን ውሳኔ የሚጠይቁ ጉዳዮች እንደተጠበቁ ሆነው ውልችን ይዋዋሊል።

የኢትዮጵያ ወንጌል አማኞች አጠቃላይ ጉባኤ የኢትዮጵያ ክርስቲያኖች ካውንስል Ethiopian Council of Gospel Believer's Churches

2. ፊርስት ፕራዮሪቲ ስቱደንት ኤንድ ዩዝ ሚኒስትሪን ስም የተከፈተውን የባንክ ሂሳብ እና ቼክ ከሂሳብ ሹሙ ጋር በጣምራ ፊርማ ያንቀሳቅሳል።
3. በጠቅላላው ጉባዔና በቦርድ የሚተሊለፍ ውሳኔዎችን ተግባራዊ ያደርጋል።
4. ፊርስት ፕራዮሪቲ ዓመታዊ የሥራ ዕቅድበማዘጋጀት ለጠቅላላ ጉባኤ ያቀርባል፤
5. የፊርስት ፕራዮሪ ፖሉሲ በማውጣት የበጀትና የሥራ ዕቅድ በማዘጋጀት ለጠቅላላ ጉባኤ ለውሳኔ ያቀርባል።
6. በመተዳደሪያ ደንቡ መሠረት ገቢ የሚገኝበትን ዘዳ ይቀይሳል፤ የፊርስት ፕራዮሪቲን ዓላማ ከግብ ሊያደርሱ የሚችሉቨስልቶችን በመቀየስ ያስፈፅማል።
7. ከሂሳብ ሹሙና ገንዘብ ያዡ የሥራ ኃሊፊነቶች ውጪ ያለትን የሥራ ድልድልች በቤተክርስቲያኒቱ አስተዲደር መመሪያ መሰረት ያዘጋጃል።
8. ሒሳብ ሹም፣ ገንዘብ ያዥና ልሎች በሥሩ የሚገኙ ሰራተኞችን እያስተባበረ እየተከታተለ እና እየተቆጣጠረ የሚኒስትሪውን የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴ ይመራል።
9. ፊርስት ፕራዮሪቲ ስቱደንት ኤንድ ዩዝ ሚኒስትሪን መተዳደሪያ ደንብ ወይንም የጠቅላላ ጉባዔ ውሳኔን በማይቃረን ሁኔታ ከቦርደ የሚሰጡትን ልሎች ተግባራትን ያከናውናል።
10. የጠቅላላ ጉባዔ እና የቦርደ ሰብሳቢ ሆኖ ያገለግላል የሚኒስትሪው ጽህፈት ቤት ያስተዲድራል
11. በሚኒስትሪው የአስተዲደር መመሪያ መሠረት ሠራተኞችን ይቀጥራል፣ ያሰናብታል።

አንቀጽ አስራ ሰባት፡ የሒሳብ ሹም ተግባርና ኃሊፊነት

ተጠሪቱ ለባለራይ ሲሆን የሚከተለትን ተግባራትና ኃሊፊነቶች ይኖሩታል፡-

1. የፊርስት ፕራዮሪ ሒሳብ ገቢና ወጪ ይቆጣጠራል፤ በትክክለኛ እንዲመዘገብና እንዲያዝ ያደርጋል።
2. የፊርስት ፕራዮሪ ሒሳብ የሚንቀሳቀስው በታወቀ የሒሳብ አመራር መመሪያ መሠረት መሆኑን ይቆጣጠራል።
3. የፊርስት ፕራዮሪቲ የባንክ ሒሳብና ቼክ ከባለ ራዩ ጋር በጣምራ ፊርማ ያንቀሳቅሳል።
4. የፊርስት ፕራዮሪ የሒሳብ መዛግብትና የተሊያዩ ሰነድችን በጥንቃቄ እንዲያዝ ያደርጋል።

አንቀጽ አስራ ሰምንት፡ የገንዘብ ያዥ ኃሊፊነትና ተግባር

ገንዘብ ያዥ ተጠሪነቱ ሊሒሳብ ሹም ሆኖ የሚከተለት ተግባራትና ኃሊፊነቶች ይኖሩታል፡-

1. ፊርስት ፕራዮሪቲ ስቱደንት ኤንድ ኡዝ ሚኒስትሪን ገቢዎች በሕጋዊ ደረሰኝ ይሰበስባል።
2. የተሰበሰበውን ገንዘብ ባንክ ገቢ ያደርጋል፣ ገቢ ያደረገበትን ደረሰኝ በጥንቃቄ ያስቀምጣል።
3. ለሥራ ማስኬጃ ለጥቃቅን ወጪዎች የሚሆን እስከ 5000 ብር ያልበለጠ መጠባበቂያ ገንዘብ ይይዛል።
4. ከሒሳብ ሹሙ ጋር የወጪና የገቢ ሒሳብ በየወሩ ያመሳክራል።
5. የፊርስት ፕራዮሪቲ ስቱደንት ኤንድ ዩዝ ሚኒስትሪን ቼክ ይይዛል።

የኢትዮጵያ የወንጌል አማኞች አጠቃላይ ጉባኤ ኅብረት ከውንስል
Ethiopian Council of Gospel Believer's Churches

6. በጣምራ ፊርማ በሒሳብ ሹመና በባለ ራዩ ሲታዘዝ ወጪ ያደርጋል።

አንቀጽ አስራ ዘጠኝ፡ የሚኒስትሪው የበጀት ዓመት

1. የፊርስት ፕራዮሪቲ ስቱደንት ኤንድ ዩዝ ሚኒስትሪ የበጀት ዓመት ከሐምላ 1 እስከ ሰኔ 30 ቀን ድረስ ይሆናል።
2. የፊርስት ፕራዮሪቲ ስቱደንት ኤንድ ዩዝ ሚኒስትሪ የአገልጋዮች ሹመት ጠቅላላ ጉባዔው ሲቀበል በዚያው ቀን ይሆናል።

አንቀጽ ሃያ፡ ያለ መግባባት ወይም የግጭት አፈታት

1. በአመራሩ ወይም በአመራሩ አባላት መካከል አለመግባባት ሲፈጠር በመተዳደሪያ ደንቡን መሠረት ጉዳዮን በመንፈሳዊ፣ ሕጋዊና ሰላማዊ በሆነ መንገድ ተወያይቶ የመጨረሻው ውሳኔ የሚሰጠው በጠቅላላው ጉባዔ ይሆናል፤
2. ሆኖም በቅድሚያ ጠቅላላ ጉባዔው የበኩሉን ጥረት በማድረግ በተቻለ መጠን መንፈሳዊ፣ ሕጋዊ እና ሰሊማዊ በሆነ መንገድ አለመግባባቶችን በማስወገድ ለችግሩ አስተዳደራዊ መፍትሔ መስጠት ይኖርበታል፤
3. በዚህ አንቀጽ ንዐስ አንቀጽ 1 እና 2 የተገለፀት እንደተጠበቁ ሆነው ያለመግባባቱ ወይም የቅሬታው ጉዳይ ባልተግባቡ ወገኖች ምርጫ እና ፈቃደኝነት በሌላ መንፈሳውያን ወንድሞች አማካኝነት እንዲታይና መፍትሔ እንዲሰጠው ሊደረግ ይችሊል።

አንቀጽ ሃያ አንድ፡ መተዳደሪያ ደንቡን ለማሻሻል

ይህ መተዳደሪያ ደንቡ በጠቅላላ ጉባዔው 3/4 ድምጽ ሊሻሻል ይችሊል፤

አንቀጽ ሃያ ሁለት፡ የሥጋ የጋብቻና የዝምድና ሁኔታ

የፊርስት ፕራዮሪቲ ስቱደንት ኤንድ ዩዝ ሚኒስትሪ ውስጥ የጋብቻ እና የሥጋ ዝምድና ያላቸው በአንድ የሥራ ዘመን በአመራርነት፣ በኃሊፊነት፣ በገንዘብ ያዥነት በጉብረት ኃሊፊነት አብረው ሊሰሩ አይችለም።

አንቀጽ ሃያ ሶስት፡ መልካም ክርስቲያናዊ ተግባራት

- በእውነትና በጽድቅ መስራት
- አንድነትን መጠበቅና በጋራ መሥራት እና መከባበርና መረዳዳት
- ትውልድን ማነጽ፣ መካሪነት፣ አባትነትና ርህራሄ
- እውነትን በፍቅር መግለፅ እና ሰላም ወዳድነት
- ለእግዚአብሔር ቃል ስልጣን መገዛት፣ በቃሉ መመራት እና መኖር
- በጎአድራጎት መሳተፍ ፡- ማለትም የተራበውን ማብሊት ፣የ[illegible] ማልበስ ፣የታረዘን

የኢትዮጵያ የወንጌል አማኞች አብያተ ክርስቲያናት ካውንስል
Ethiopian Council of Gospel Believer's Churches

- ማልበስ፤ አረጋዊያንን መርዳት መንከባከብ ፤ወላጆቻቸውን በሞት ምክንያት ያጡትን ማሳደግ ማስተማር ፤ ልጆቻቸውን የትምህርትቤት ክፍያ ከፍለው ማስተማር ያልቻሉትን ከፍያን እየከፈሉ ማስተማር፤ የትምህርት ቁሳቁስ ማቅረብ፤ የትምህርት ቤት አልባሳት ማሟላት፤ እንዱሁም በከተማና በገጠር የልማት ስራዎችን መሥራት ።
- በየወረዳው የሚገኙ የወጣት ማህበራትን መሪዎችን በነጻ የመሪነት ክህሎት ማስልጠን
- በት/ቤቶች ስለ ልህቀት ከየት/ቤት አስተዳደር ጋር በመተባበር ማስልጠን
- የሱስ አስከፊነትን የሚያሳይ ጥናቶችን ማቅረብ
- በሱስ የተጠቁ ወጣቶችን ካሱስ ነጻ የሚሆኑበትን መንገድ ማሳየት
- ለወላጆች ልጆች አስተዳደግ ስልጠና መስጠት
- በመንግስት በተፈለግንበት ሁሉ በጎ ፈቃድኛ ሆነን እናገልግላለን
- የተለያዩ ጥናቶችን ማድረግ

አንቀጽ ሃያ አራት፡ ተፈፃሚነት

የፈርስት ፕራዮሪቲ ስቱደንት ኤንድ ዩዝ ሚኒስትሪ አመራርና አባላት ሁለ ላይ ተፈፃሚ የሚሆን ይሆናል።

አንቀጽ ሃያ አምስት፡ መተዲደሪያ ደንቡ በሚፀናበት ጊዜ

ይህ መተዲደሪያ ደንብ የሚፀናው በጠቅላላ ጉባኤ ጽድቆ የኢትዮጵያ የወንጌል አማኞች አብያተ ክርስቲያናት ካውንስል ቀርቦ ከተመዘገበበት ጊዜ ጀምሮ የሚኒስትሪው መተዲደሪያ ደንብ ሆኖ በሥራ ሊይ ይውላል።

እግዚአብሔር ኢትዮጵያን ይባርክ